
هل الله اصبح إنسانا ؟

# አምላክ ሰው ሆኗልን?

በ ቼዎን እስታርስ




# መግቢያ

ለሁሉም ጸጋው አላህ ሱብሀነሁ ወተአላ የአለማቱ ጌታ ምስጋና ይገባው።(quran 1:2)

በአላህ ፍቃድ ይህን ጽሁፍ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ሌሎች ሀይማኖቶች ከእስልምና የሚለዩበት ትልቁ እና የመጀመርያው ነጥብ አምላክ በሰው መልክ ወይም በፍጡራን ውስጥ ተገልጹዋል የሚለው በመሆኑ ነው። ስለዚህ “ Did GOD become Man?” የሚለውን የዶክተር ቢላል ፍሊፕስን መጽሃፍ መሰረት አርጌ ትንሽ እንኳን ቢሆን ለእውነት ፈላጊዎች መንገድ ትሆን ዘንድ አቅርቤላቹሃለው። ከሞላ ጎደል በገለልተኝነት እና ውሳኔውን ለአንባቢ በመተው እንደጻፍኩ አምናለው። ይህንን ጽሁፍ (ከሽያጭ ውጭ) ያለኔ ፍቃድ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት ይቻላል። አላህን በልፋቴ ልክ ሳይሆን በኒያዬ ልክ እንዲመነዳኝ ጠይቀዋለው። እህት ወንድሞቼ በዱዐ እንዳትረሱኝ አደራ እላቹሃለው።

የአላህ ሰላም እና እዝነት ቅኑን መንገድ ለተከተሉት ሁሉ ይሁን።

# አምላክ እና የሰዎች አመለካከት

በርካታ ሳይንቲስቶች ፈጣሪ በሰዎች አእምሮ ውስጥ የተፈጠረ ማንነት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። “ፈጣሪ የለም ሁሉም በዝግመተለውጥ ነው የተፈጠረው” የሚለውን የዳርዊንን አስተሳሰብ ሚከተሉም በርካቶች ናቸው።

በሌላ በኩል ከእስልምና ውጭ ያሉት ሃይማኖቶች አምላክን ማምለክ በሚል ምክንያት ጣዖታትን እና ምስሎችን ለአምላክ ማድረግ የእምነታቸው ክፍል አድርገውታል። በተለይ የ ሂንዱዊዝም እምነት ፥ የሚያስተምረው አንድ ሃያል አምላክ መኖሩን ቢሆንም አምላክ በተለያዩ ነገሮች ተገልጿል የሚል እምነት ስላላቸው የተለያዩ አማልክቶችን ቀርጸው ያመልካሉ። ቀደምት የግብጽ እና የሮማ እምነቶች ጣዖት አምልኮን ካስተናገዱት ውስጥ ናቸው።

በዚህ መጽሃፍ የምንዳስሰው የጣዖት አምልኮን ሳይሆን “አምላክ ሰው ይሆናል” የሚለውን እምነት ነው።

# ሰው አምላክ ነው

በሂንዱዊዝም እምነት ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ሁሉም ነገር አምላክ ነው። በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ውስጥ አትማን ሚባል መንፈስ አለ ፤ መንፈስ ደግሞ ብራህማን ወይም አምላክ ነው፤ ስለዚህ አትማን እና ብራህማን አንድ ናቸው ብለው ያምናሉ። በተጨማሪም ማህበረሰብን በመደብ ይከፋፍላሉ። ማህበረሰብ ከተለያዩ የመለኮት አካል እንደመጡ ያምናሉ። ለምሳሌ የላይኛው መደብ ብራህማኖች ከፈጣሪ ራስ ፤ ዝቅጠኞቹ ሱድራስ ደግሞ ከፈጣሪ እግር እንደተገኙ ያስባሉ። ታውቂዎቹ መደቦች አራት ብቻ ቢሆኑ በስራቸው ግን በሺዎች ሚቆጠሩ በርካታ ጎሳዎች አሉ። ሂንዱዎች ሰው ሲሞት መንፈሱ በሌላ አካል ዳግም ይወለዳል ብለው ያምናሉ። “አትማን ሚባለው መንፈስ በጭራሽ አይሞትም ይልቅ እንዳዲስ ይወለዳል። በዚህኛው ሂወት ጥሩ ሰው ከሆኑ በቀጠዩ ህይወት ከፍ ካለው መደብ ወይም ብራህሚን ይወለዳል፤ መጥፎ ከሆነ ግን ዝቅተኛ ከሆኑት ሱድራስ ይወለዳል” የሚል አስተምህሮ አላቸው። በዚህ ምክንያት በየጊዜው ሰዎች ራሳቸውን ያጠፋሉ። ሰዎች የዚህ አይነት እምነት ሲኖራቸው ራስን ማጥፋት ቀላል ይሆንላቸዋል። የአትማን መንፈስ ዳግም እየተወለደ በመቀጠል ከብራህሚን ከተወለደ ቡሃላ የዳግም መወለድ ሂደቱ ያበቃና ከብራህማን ጋር ይዋሃዳል። የመዋሃድ ሂደቱን ሂንዱኮች “ሞክሻ” ሲሉት ቡድሂዝሞች (የቡድሃ አምላኪዎች) ደግሞ “ኒርቫና) ይሉታል። ስለዚህ ሰው አምላክ ይሆናል ብለው ያምናሉ።

# አምላክ ፍጡራኑን ሆኗል

አምላክ የሰው ስጋ ለብሶ መጣ የሚለው የክርስትና አስተምህሮ በጥንታውያኑ ግሪኮች ዘንድ መሰረት አለው።አምላክ ስጋ ለብሶ መጣ የሚለው አባባል በዩሃንስ ወንጌል ፡፡1 እና ፡፡14 ላይ ይገኛል። “ በመጀመርያ ቃል < ሎጎስ> ነበር ። ቃልም እግዚአብሄር( ho theos ) ዘንድ ነበር። ቃልም እግዚአብሄር (ton theos) ነበር።... ይልና 14 ላይ ቃልም ስጋ ሆነ ይላል። ሎጎስ “ቃል” ተብሎ ቢተረጎምም ሎጎስን ግን በትክክል አይገልጽም። “ሎጎስ” የሚለው ቃል ለመጀመርያ ጊዜ የተገኘው በሄራክሊተስ(540-480 BC) ንግግር ውስጥ ነው። በአርስቶትል ጊዜ አላስፈላጊ ከሆነ ተፈጥሮአዊ ሃይል ተተክቶ ምድራዊ ሃይል ሆነ። ሎጎስ የሚለው ቃል በድጋሚ የ እምነት መሰረታቸውን ሎጎስን እና አምላክን ባደረጉት በስቶኪዎች ስርአት ውስጥ ብቅ አለ። ፊሎ በመባል የሚታወቁት አይሁዳዊው የአለክሳንደርያ ፈላስፋ የብሉይ ኪዳኑን ቃላት ከስቶይኪዎች ሎጎስ ጋር አያይዞ ገልጾታል። ከዛን ጊዜ ቡሃላ ሎጎስ አምላክ ራሱን ለአለም ሚገልጽበት መንገድ እንሆነ ታመነ። (Dictio. of philo. And religion,p.314.)

ይህ እምነት ምክንያት ያስፈልገው ስለነበር የሃጥያት ውርስና መለኮታዊ መስወአት የሚባሉት ጽንሰሃሳቦች ተፈጠሩ። “ በአዳም ሃጥያት ምክንያት ሰው ሁሉ በውርስ ሃጥያቱ ሞተ ፤ ይህ ሞት እንዲቆም መለኮታዊ መስወት ያስፈልገዋል ተባለ። በዚህ ምክንያት አምላክ አምላክም ሰውም የሆነውን ልጁን ከሰው ወለደ። በስተመጨረሻም ልጁ ለሰዎች ተሰቅሎ በመስቀል ላይ ከሞተ ቡሃላ ዳግም ተነስቶ አረገ ። አሁን በአባቱ ቀኝ የፍርዱን ቀን እየጠበቀ ይገኛል” ይሉናል። ስለዚህ ከሰው ልጆች አንድ አምስተኛ የሚሆኑት ክርስትያኖች በአለም ታሪክ ውስጥ አምላክ ሰው ሆኗል ፤ ስጋ ለብሶ መምጣቱን መቀበል ለመዳን አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ።

## ሰዎች አምላክ ይሆናሉ

ከክርስትና አስተምህሮ በተጨማሪ ልክ እንደ ሂንዱዊዝሞች እና ቡድሂዝሞች* ሰዎች አምላክ መሆን ይችላሉ ብለው የሚያምኑ የ እስልምና ክፍሎችም አሉ።

* ( ቡድሂዝሞች የቡድሃ አምላኪዎች ናቸው። ቡድሃ በዚህ ምድር ላይ ሲኖር የነበረ አስተማሪ ነበር።ከሞተ ቡሃላ ሰዎች በሰው የተገለጸ አምላክ ነው ብለው በማመን ጣዖቱን ሰርተው እሱን ማምለክ ጀመሩ)

የእምነታቸው መሰረት ከምስቲሲዝም የተገኘ ሲሆን ምስቲሲዝም ከጥንታዊው ሚስጥራዊ የግብጽ እምነቶች አንዱ ነው። የእምነቱ አስተምህሮ አምላክን በጸምና በጸሎት ማግኘት ይቻላል የሚል ነው። ሚስቲሲዝም የሰዎች ትልቁ አላማ ይህን ውህደት ማግኘት እና ከ አምላክ ጋር መዋሃድ እንደሆነ ያስተምራል። የግሪኩ ፈላስፋ ፕሉቶ በሲንፖዚየሙ ውይም ጉባኤው ውስጥ ይህንን ሃሳብ አቅርቧል። እንዲሁም የሰው ልጅ መንፈስ ከአምላክ ጋር ዳግም አንድ እስከሚሆኑ ድረስ እንዴት የመንፈሳዊነት ደረጃን እንደሚጎናጸፉ አብራርቷል።(colliers Encyclopedia,vol.17,p.144)

የዚህ አስተምህሮ መሰረት የሰው ልጆች በምድራዊው አለም ላይ በሰውነት አካል ውስጥ የተጠመዱ የፈጣሪ አካላት ናቸው የሚለው አመለካከት ነው። በነሱ እሳቤ “ የሰዎች መንፈስ መለኮታዊ ነው። በዚህ ምድር የተጠመደው የፈጣሪ አካል ራሱን ከምድራዊው አለም ነጻ አውጥቶ ከአምላክ ጋር መዋሃድ አለበት።”

ከእስልምና ክፍሎች ውስጥም ተመሳሳይ ሃሳብ የሚያራምዱ ክፍሎች አሉ። ተከታዮቹ በተለምዶ “ሱፊ” ይባላሉ። የእምነት ስርአታቸውም ሱፊዝም ይባላል። ሱፊዎች በተለያዩ ክፍሎች(ጠሪቃህ) ተሰንጥቀዋል። እያንዳንዱ ክፍልም በመስራቹ ስም ነው የተሰየመው። አብዛህኞቹ ክፍሎች ለተከታዮቹ የሚጠበቅባቸውን መንፈሳዊ ፣ ሀይማኖታዊና አካላዊ እንቅስቃሴ ካደረጉ ቡሃላ ከአምላህ ጋር አንድ እንደሚሆኑ ያስተምሯቸዋል። ይህ አንድነት በአረብኛው “ፋና” ወይም “ዉሱል” በመባል ይታወቃል። ( ኡሉሙዲን ቅጽ 4, ገጽ 212)

ከአምላክ ጋር አንድ መሆን የሚለው አመለካከት እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ምሁራኖች ቢወገዝም በብዙሃኖች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል። አል ሀላጅ(858-922) የተባለው የሱፊ አማኝ አምላክ ነኝ ብሎ ባደባባይ በማወጅ፤ ግጥም እና “አተዋሲን”የሚባል መጽሃፍም ጽፏል። በመጽሃፉ ውስጥ “ እኔ የመጨረሻው ፍጹም እውነት ነኝ። ምክንያቱም በእውነቱ ምክንያት ዘላለማዊ እውነት ነኝና። ጓደኞቼና መምህራኖቼ ኢብሊስ እና ፈርዖን ናቸው። ኢብሊስ በጀሃነም ቢቀጣም በሱና በአምላክ መካከል ያለውን ነገር አልገለጸም። ብሞትና ብሰቀልም እጆቼና እግሮቼንኳ ቢቆረጡ ሃሰት ነው ብዬ አልተውም።” (idea of personality,p.32)

# ለምን?

የጥንት ሰዎች አምላክ ሰው ሆኗል ወይም ሰው እና አምላክ አንድ ነበሩ ብለው አንዲያምኑ ያደረጋቸው ነገር ምንድነው? ትልቁ ምክንያት አምላክ ይህን ፍጥረት ከምንምነት አንስቶ እንደፈጠረ አለመረዳታቸው ነው። ወይም አምላክ ልክ እንደነሱ ካሉ ነገሮች ነገሮችን እንደሚፈጥር ማሰባቸው ነው። ለምሳሌ ያህል ሰዎች እንጨት ገጣጥመው ወንበር እና ጠረጴዛዎችን ይሰራሉ፤ እንዲሁም ከአፈር የተለያዩ የሸክላ እቃዎችንና ቤቶችን ይሰራሉ። ነገር ግን ወንበሩን የሰሩበት እንጨትም ሆነ ቤቱን የሰሩበት አፈር እነሱ የፈጠሩት አይደለም። በዚህ ምክንያት አምላክም ልክ እንደነሱ ካለ ነገር እንደፈጠራቸው ያስባሉ። ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ላይ አምላክ ሰዎችን በራሱ አምሳል አንደፈጠረ ይናገራል ። በሂንዱዊዝምም ፕሩሳ በሰው አምሳል ያለ ፈጣሪው አምላክ ብራህማ ሲሆን በሺዎች ሚቆጠር አይን እና ጭንቅላት ያለው ትልቁ የብራህማ ልጅም ነው። ቪራጅ ደግሞ ከሱ የተገኘች ስትሆን በፍጥረት ሂደት ውስጥ የሱ ተጓዳኝ ሴት ነች።

ባጠቃላይ የሰው ልጅ የማስተንተን እና የመረዳት አቅሙ ደካማና የተገደበ ነው። ገደብ የሌላቸውን ነገሮች መረዳት አይችሉም። አምላክ ለአደም ያስተማርው ፍጥረታትን ከምንም ነገር እንደፈጠረ ነው። አንድን ነገር መፍጠር በፈለገ ጊዜ ሁን ይለዋል፤ ይሆናልም። አምላክ ፍጥረታትን ከራሱ ነው የፈጠረው የሚለው አመለካከት ፈጣሪን ወደፍጡራን ደረጃ ዝቅ ያደርገዋል። እንዲህ የሚያስቡ ሰዎች የአምላክን አንድነት እና ብቸኝነት(እሱን ሚመስልል ምንም እንደሌለ) አይረዱም። ፍጥረትን ከራሱ ቢፈጥር ኖሮ እንደፍጡራኑ በሆነ ነበር። ወይንም ፍጡራን ከአምላክ ጋር በተመሳሰሉ ነበር።

# አምላክ ሰው ሆኗል?

የሚቀረው ጥያቄ አምላክ ሰው ሆኗልን? የሚለው ነው። ሎጂካሊ መልሱ አልሆነም ነው። ምክንያቱም አምላክ ሰው ሆነ የሚለው ጽንሰሃሳብ በራሱ ሰዎች አምላክ የሚሉትን እና አምላክ ሁሉን ነገር ማድረግ ይችላል የሚለውን ጽንሰሃሳብ ይቃረናል። በክርስቲያኖች መጽሃፍ ቅዱስ ላይም

“በእግዚአብሄር ዘንድ ግን ሁሉም ይቻላል” ተብሎ ተጽፏል። ማቲ.19:29

እንዲሁ በቁርዐን ላይ

﴿ إِن الله علي كل شيء قدير ﴾

{ አላህ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው። } በቀራህ 2:20

በርግጥም አምላክ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው። ነገር ግን ቻይ ነው ስንል ግልጽ ሊሆንልን ሚገባ ነገር አለ፤ ማለትም አምላክነቱን በማይጸረር መልኩ እንጂ በደፈናው ማየት የለብንም። አምላክ የሁሉ ነገር ፈጣሪና ጀማሪ ከመሆኑም በላይ የመጀመርያውና የመጨረሻው እንዲሁም ዘልአለማዊ አምላክ ነው። አምላክ ሁሉን ነገር ማድረግ ከቻለ መሞት ይችላልን? ብሎ መጠየቅ ሞኝነት ነው ።

ምክንያቱም ዘልአለማዊነቱን መቃወም ነው እንዲሁ እርሱ ሊያነሳው የማይችለውን ድንጋይ መፍጠር ይችላልን? ብሎ መጠየቅ ቂልነት እና በተዘዋዋሪ ከሱ ትልቅ የሆነን ነገር መፍጠር ይችላልን ብሎ እንደመጠየቅ ነው። አምላክ ሰው ይሆናልን? ወይም ይወለዳልን? ብሎ መጠየቅም እንዲሁ አምላክ ጅማሬ አለው? ብሎ እንደመጠየቅ ነው። አምላክ ይወለዳል ካልን ሚወልደው እና ሚፈጥረው አካል ያስፈልጋል ፤ይህም የፈጣሪን አምላክነት ይቃረናል። ሰው ይሆናል ካልን ከሁሉ ቻይነት ወዳለመቻል ወይም ደካማነት ማምጣት እንደመፈለግ ነው። ስለዚህ አምላክ ሁሉን ቻይ ነው ስንል አምላክነቱን በማይንድ መልኩ ነው። ፈጣሪ በጭራሽ ራሱን አይፈጥርም ፍጡርም አይሆንም።

# ሰው አምላክ መሆን ይችላል?

ፍጡራኖች ከአምላክ በተቃራኒ ካለመኖር ወደመኖር የመጡ ናቸው። ለመኖርም መብላት ፣ መጠጣት ፣ መተኛት እንዲሁም መራባት አለባቸው። በስጠመጨረሻም ይሞታሉ። እነዚህ ሁሉ ለአምላክ ማይገቡ ባህሪያት ናቸው። አምላክ ይህን ካረገ ከፍጡራኑ ጋ ተስተካከለ ማለት ነው። በተመሳሳይ ሰዎችም አምላክ መሆን አይችሉም ። አለመሞትና መፍጠር አይችሉም። የሰው መንፈስ መለኮታዊ ነው ማለት ሰው አምላክ መሆን ይችላል ወደማለት ይወስዳል።

የቀደምት ግሪኮችን ፣ የክርስትያኖችን ፣ የሂንዱዎችንና የሱፊዎችን እሳቤ ብንከተል የሰው ልጆች ሀጥያት ሲሰሩ አምላክ የሆነ ጊዜ የሱ አካል የነበረውን አካል ነው ሚቀጣው ወደሚል ትርጉም አልባ አመለካከት ይወስደናል። የሰው ልጅ ነብስ ጥሩና መጥፎ የመስራት ነጻ ምርጫ ካለው በተመሳሳይ ሰአት አምላክ ሊሆን አይችልም። አልያም እያንዳንዱ ሰው አምላክ ነው ለማለት ያስገድዳል።

# አምላክ ልጅ አለው?

አምላክ ሰው አይሆንም ብለናል፤ ልጅስ ሊኖረው ይችላል? አንዳንዶች አምላክ ሁሉ ነገር ማድረግ ከቻለ ልጅ ሊኖረው ይችላል ብለው ያስባሉ። ግን እስኪ አስቡት፤ ሰዎች እነሱን ሚመስል ትንሽ ህጻን ይወልዱና እሱም ሲያድግ እሱን ሚተካ ልጅ መውለድ ይጀምራል። ውሾችም ቡችሎችን ዶሮዎችም ጫጩቶችን ይፈለፍላሉ። አምላክ ከወለደ መውለድ ያለበት ልክ እንደሱ ያለ አምላክ ነው። ግና አምላክ ከወለደ የተወለደው በጭራሽ ከወለደው አምላክ ጋር ሊመሳሰል አይችልም ምክንያቱም ሃያሉ አምላክ ወይም ክርስትያኖች አብ የሚሉት በጭራሽ አልተወለደም ፤ ጅማሬም እናትም የለውም። አምላክ ልጅ ካለው ቢጤ ወይም አጋር ኖረው ማለት ነው። አምላክ ደግሞ አንድም ቢጤ የለውም።

ከአምላክ ውጭ ያለው ነገር በሙሉ በሱ ትእዛዝ የተገኙ ናቸው። ምንም ያህል የሠው ልጅ ከምንም ነገር እንዴት እንደተፈጠረ ማወቅ ባይችልም የሆነውም  የሚሆነውም ግን እንዲሁ ነው። የሱ አፈጣጠር ከፍጡራኑ ፍጹም የተለየ ነው።

በፈጣሪ የተላኩት እውነተኛ ምልእክተኞች እና ነብያቶች አስተምህሮም እንዲሁ ነው። የአላህ ሰላም በነሱ ላይ ይሁንና የኢብራሂምም የሙሳም የኢሳም የምናውቃቸውና ያላወቅናቸው ነብያቶች ምልእክትም ይኸው ነው። ነገር ግን ይህ አስተምህሮ  አሁን ሚገኘው በቁርዐን ላይ ብቻ ነው። ምክንያቱም እስካሁን ሳይበረዝ ሳይከለስ የቀድሞ ይዘቱን ከ 1400 አመታት በላይ ይዞ የቆየው ቁርአን ብቻ ነው።

# እሱን የሚመስል ምንም የለም (ሱረቱ ሹአራእ 11 ) (لَيسَ كمِثلِهِ شَيءُ )

✓ለራህማን ልጅ ሊኖረው አይገባም። ( መርየም 92)

✓አንድን ነገር በሻ ጊዜ እንዲሆን ያዘዋል፥ ይሆናልም። ( አስ ሲን 82)

✓አላህ ምንም ልጅ አልያዘም።ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም። የዛን ጊዜ አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለያየ ነበር።ከፊላቸው በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር።አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ። (ሙእሚኑን 91)

✓ወይስ ያላንዳች(ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነሱ ፈጣሪዎች ናቸውን? (ጡር 35)

አላህ ኢሳ ዐ.ሰ እና መርየም ሰዎች እንደሆኑ በቀላሉ እንዲህ ብሏል፡- ﴿ ምግብ ይበሉ ነበር ﴾ (ማኢዳ 75)

አምላክ ሰው አይሆንም የሚለው አስተምህሮት መሰረታዊ ነው። ምክንያቱም እስልምናንና የተቀሩትን ሃይማኖቶች የሚለይ መሰረት ነው። ሌሎች እምነቶች በዚህም ሆነ በ ሌላ መልኩ የአምላክን ማንነት ንደውታል። አምላክ ሰው ይሆናል ወይም ሰው አምላክ ይሆናል ብሎ ሰውን ማምለክ ትልቅ ሃጥያት ነው። መሰረታዊ ጉዳይም ነው። ምክንያትም ለመዳን የአምላክን በብቻነት አምላክ መሆን መቀበል ያስፈልጋል። በርግጥ ማመን ብቻ አያድንም፤ እምነቱ በመልካም ስራ መረጋገጥ እና መገንባት አለበት። (ሱረቱል አስር 1-4). ከሞላጎደል ዋናው ነጥብ አምላክን ማወቅና አምላክ ሰው ሆኖም ወደፊትም እንደማይሆን ማወቅ ነው።

# እየሱስ ሰው ብቻ ወይስ ሰውም አምላክም ?

የ ክርስትና እምነት ተከታዮች አምላክ አንድም ሶስትም ሲሆን አብ የእየሱስ አባት ፥ ወልድ ወይም እየሱስ ደግሞ የአብ ብቸኛው ልጅ ወይም የወለደው ልጁ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከአብ የሰረጸ መንፈስ እንደሆኑ እነሱም ሶስት ሳይሆኑ አንድ አምላክ ብቻ ናቸው ብለው ያምናሉ። አብና ወልድ አንድ ናቸው ነገር ግን አብ ወልድ አይደለም ፥ ወልድም አብ አይደለም ብለው ያምናሉ። ወልድ የሰውን ልጅ ለማዳን በሰው አምሳል ከማርያም የተወለደ አምላክ ነው ብለው ያምናሉ። ከሰው ስለተወለደ ሰው ከአምላክ ስለተወለደ አምላክም ነው ብለው ያምናሉ። ማለትም በነሱ እምነት ወልድ በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ሰው ሆኖ ኖረ ለሰው ልጅ ሲልም ተሰቅሎ ሞተ፤ ከሞትም አባቱ አነሳው፤ ወዳባቱ ካረገ ቡኃላ በቀኙ ተቀምጦ ለፍርዱ ቀን በካዱት ላይ ሊፈርድ እየጠበቀ ነው። ዳግም እዚህ ምድር ላይ ሊፈርድ በትንሳኤ ይመጣል ፤ያኔ ፍጻሜ ይሆናል ይላል አስተምህሮቱ።

በአጭሩ የክርስትና አስተምህሮ መሰረት የአምላክ በሰው አካል(እየሱስ) መምጣት እና መሰቀል ማመን ነው። ስለዚህ ረጋ ባለ መንፈስ ሁሉንም እንመርምር። አዳም የዛፉን ፍሬ ሲበላ አምላክ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንኃለው ብሎታል???????

# ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለው ?????

ዘፍጥረት ፡26 ላይ እንሂድ ፡- እግዚአብሄርም አለ ፡-ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር...

ጥ.1 በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ሲል ምን ማለቱ ነው?

ጥ.2 ሰዎች በአብ ? ወይስ በወልድ ? ወይስ በመንፈስ ቅዱስ አምሳል ነው የተፈጠሩት?

ጥ.3 እየሱስ አዳም ሳይፈጠር በፊት ነበርን? አምላክስ ነበር? በአምላክነቱስ ተገልጿል? ስልጣንስ ነበረው? የአብ ልጅስ ነበር ያኔም ?

አዲስ ኪዳን ላይ እየሱስ ጥበብ ተብሏል፤ እንዲሁም በ መጽሃፈ ሲራክ ላይ “ከሁሉ ቀድማ ጥበብ ተፈጠረች” የሚል ነገር እናገኛለን። እየሱስ ወይም ጥበብ ለምን ተፈጠረ? ይህ የእየሱስን በኩር ፍጡርነት ያሳያል?

እነዚህ ጥያቄዎች በኔ ሳይሆን በናንተ በአንባብያን የሚመለስ ጥያቄ ነው። አዳም ከተፈጠረ ቡኃላስ ?????

ዘፍጥረት “16 ፦ እግዚአብሄር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው። ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለኽ፤17 ነገር ግን መልካምና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ።ከርሱ የበላህ ቀን ሞትን ትሞታለኽና።” አለው እባቡም አሳስቷቸው ከበሉ ቡሃላ እግዚአብሄር ምን አላቸው? ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለው አለው??? በጭራሽ በጭራሽ አንድም ጊዜ መጽሃፍ ቅዱስ ላይ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለው አላለውም። ታድያ ይህ አስተምህሮት ኬት መጣ???

አምላክ ለምን ከገነት አስወጣቸው?? እዛው ዘፍጥረት ፡22 ላይ “ እግዚአብሄር አምላክም አለ፦ እንሆ አዳም መልካምና ክፉን ለማወቅ ከኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞም ከህይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ለዘልአለም ህያው ሆኖ እንዳይኖር...

ጥ.5 ከኛ እንደ አንዱ ሆነ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ከዘፍጥረት እንደምንረዳው አምላክ አዳምን ከገነት ያባረረው እንደ አምላክ እንዳይሆን ነው።

አዳምና ሄዋን ከዛፉ ከበሉ ቡሃላ ምድር ላይ ለፍተው እንዲኖሩ ፈርዶባቸዋል። ምድር ላይም ተዋለዱ ... ታድያ ወደገነት መመለሻው መንገድ የትኛው ነው። አምላክ ሰው ሆኖ መዶ በመሞት ወይስ ሰዎች መልካም ስራ ሰርተው በመሞት???

በመጽሃፍ ቅዱስ  ብዙ ቦታ ላይ አምላክ ሰው አለመሆኑን ይናገራል። ለምሳሌ ዘኁልቁ 23፡19 ላይ

“ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሄር ሰው አይደለም ፥ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም።”

አምላክ ሰው አንዳልሆነ ይህ አንቀጽ ብቻውን  በቂ ነው። ሌላም መጨመር ይቻላል ግን ክርስትያኖች አምላክ ሰው ያልሆነው በብሉይ ኪዳን እንጂ በሐዲስ ኪዳን አይደለም ። አምላክ ሰው አይደለም ማለት አይሆንም ማለት አይደለም ይላሉ ነገር ግን አምላክ ሰው የሆነ እለት ይህን ቃሉን እንደሚጣረስ እንዲሁም አምላክነቱ እንደሚያበቃለት ልብ ልንል ይገባል። ምክንያቱም ሰው መልሶ አምላክ መሆን አይችልምና። መጽሃፈ እዮብ 25፡4 ላይ ሰውስ በእግዚአብሄር ፊት ጻድቅ ይሆን ዘንድ፥ ከሴትስ የተወለደ ንጹህ ይሆን ዘንድ እንዴት ይችላል...6፤ይልቁንስ ብስብስ የሆነ ሰው፥ትልም የኾነ የሰው ልጅ ምንኛ ያንስ! ይለናል። ሁላችንም እንደምናውቀው እየሱስ ከሴት ነው የተወለደው። ታድያ አምላክ ሰው እንዴት ይሆናል እንዴትስ ብስብስ እና ትል ሆነ እንላለን ? ከየት አምጥተን ? ማስረጃ አለን ?

እየሱስ ብዙ ጊዜ የሰው ልጅ ተብሏል። ለምሳሌ ማቲ. 26፡24 እና ማር. 14፡21ን ማየት እንችላለን። ክርስትያኖች እየሱስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው ብለው ያምናሉ።

እንዲሁም እየሱስም እራሱን የሰው ልጅ ብሎ ጠርቷል። ነገር ግን አንድም ጊዜ ራሱን አምላክ ብሎ አልጠራም። ሆኖም የእግዚአብሄር ልጅ እና ጌታ የተባለበትን ቦታዎች ከመጽሃፍ ቅዱስ በቀላሉ ማግኘት እንችላለን። አብን አባት ብሎ ሲጠራም ብዙ ቦታ ላይ እናገኛለን። እየሱስ (ዐ.ሰ) በርካታ ተአምራትንም ሰርቷል። ከዚህ ተነስተን እየሱስ አምላክ ነው ማለት እንችላለን? ሁሉም እየሱስ አብ እንዳልሆነ ያውቃል ፤ ወልድም መንፈስ ቅዱስ እንዳልሆነ ያውቃል። ማንም ክርስቲያን እየሱስና አብ አንድ ናቸው አይልም። ነገር ግን እኔና አብ አንድ ነን (ዩሀ.10፡30) ስላለ እየሱስን አምላክ ነው ማለት እንችላለን? በምድ ሳለ እየሱስ ፍጹም ሰው ከነበር እኔና አብ አንድ ነን ከሚለው ይልቅ አንድ እንሆናለን የሚለው ይበልጥ አግባብ አይሆንም?

# የ አምላክ ልጅ ስለሆነ...

ሎጂካሊ ካየነው የሰው ልጅ ሰው ሲሆን የ ውሻ ልጅም ውሻ ነው ሚሆነው። እንዲሁ የ አምላክ ልጅም አምላክ ነው መሆን ያለበት። ነገር ግን መውለድም ሆነ መወለድ የአምላክን ማንነት ይጻረራል። አምላክ ከተወለደ እናት እና አባት ይኖረዋል። እንደወላጅነታቸውም ከ ልጅ አምላክ ይበልጣሉ። በአጭሩ እንደፍጡራን ለአምላክ ቤተሰብ አደረግን ማለት አይደል?

በፊጠራ አለም ውስጥ ቫምፓየር ሚባል ነገር አለ። ቫምፓየር ከሰው ልጅ ላይ ልጅ ከወለደ የተወለደው ልጅ ግማሽ ሰው ግማሽ ቫምፓየር ይሆናል። ቫምፓየርን መግደል ሚችለው ከሰው የተወለደ ቫምፓየር ብቻ ነው። በፊልምና ልቦለድ አለም ውስጥ ከመለመዱ የተነሳ የሰው ልጅ አእምሮ ሁለት የተጋጩ ማንነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ መቀበል ጀምሯል። ግን እንዴት ሰው የሰው ደም ሚጠጣና ለሰው ፍቅር ያለው ፍጡር በአንዴ ይሆናል??? ላመጣላቹ የፊለኩት ነጥብ እንዴት አምላክ በተመሳሳይ ሰአት ያልተፈጠረ እና ፍጡር በአንዴ ይሆናል?? ተፈጥሯልም አልተፈጠረምም፤ አምላክ ነው አምላክም አለው መልሱ ደግሞ ከአምላኩ ጋር በፍጹም ማይለይ አንድ አምላክ ነው ማለት እስኪ ምነኛ ይሆን??? ሞቷል ግን አልሞተም እሚባል ቋንቋ ሚገባው አለ?? እስኪ በመጀመርያ የአምላክ ልጅ መባሉ አምላክ ያረገዋልን እሚለውን ነጥብ አብረን እንይ...

# ❖ ነጥብ አንድ ፦ የአምላክ ልጅ የተባለው እሱ ብቻ አይደለም

በባይብል ውስጥ የአምላክ ልጅ የተባሉ ብሱ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ ያህል በዖሪት ዘጸአት 4፡22-23 ላይ { ፈርዖንንም እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፦ 23 ፤ እስራኤል የበኩር ልጄ ነው...}

እንዲሁም በመዝሙረ ዳዊት 89፡26-27 [ ርሱ አባቴ አንተ ነህ አምላኬ የመድኀኒቴም መጠግያ ይላል። 23፤ እኔም ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ ፥ ከምድርም ነገስታት ከፍ ይላል።]

እንዲሁም ሰለሞንን ልጄ ይለዋል። (2 ሰሞ.8፡22-23)

በብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በአዲስ ኪዳንም የአምላክ ልጅ የተባሉ አሉ። ለምሳሌ በሉቃስ ወንጌል 3፡38 ላይ የእየሱስን የዘር ሃረግ እየዘረዘረ መቶ [... የሴት ልጅ፥ የአዳም ልጅ፥ የእግዚአብሄር ልጅ ] ይላል።

አንዳንዶች የእየሱስ ልጅነትና የሌሎቹ ይለያያል፤ምክንያቱም እየሱስ የወለደው ልጁ ነው ይላሉ። ነገር ግን በመዝሙረ ዳዊት 2፡7 ላይ [ ትእዛዙን እናገራለሁ ፤ እግዚአብሄር አለኝ፦ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድኩህ።]

በዩሃንስ ወንጌል 1፡13 [ እነርሱም ከእግዚአብሄር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከስጋ ፍቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም። ]

# ❖ ነጥብ ሁለት፡-የማስረጃዎቹ አወዛጋቢነት

ምንም ያህል እየሱስ ራሱን የሰው ልጅ እያለ ቢጠራም አንድም ቦታ ላይ ግን ራሱን የአምላክ ልጅ ብሎ ጠርቶ አያውቅም። ሆኖም በወንጌሎቹ ውስጥ ብዙ ቦታላይ የአምላክ ልጅ ተብሏል። እስኪ ቀለል አርገን እንገምግማቸው። ወንጌሎቹን በጥልቀን እና በንጽጽር ካየናቸው ከአራቱ ወንጌላት የማቲዎስ ወንጌል እየሱስን የአምላክ ልጅ አድርጎ ያቀርበዋል። ነገር ግን ሌሎቹን ካየነው በማቲዎስ የተተረከውን አናገኝም። ለምሳሌ በማርቆስ ወንጌል 15፡29-30 [ የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበረና ዋ ቤተመቅደስን የምታፈርስ በሶስት ቀንም የምትሰራ ከመስቀል ወርደህ ራስህን አድን አሉ። ] እዚጋ ልብ ካልን ሰዎቹ የአምላክ ልጅ ከሆንክ አላሉትም ። ነገር ግን ማቲዎስ 27-40 ጋር ከሄድን [ቤተመቅደስን የምታፈርስ በሶስት ቀንም የምትሰራው ራስህን አድን፤ የእግዚአብሄርስ ልጅስ ከሆንኽ ከመስቀል ውረድ አሉት።] የሚል ነገር እናገኛለን። እንደምናየው ማቲዎስ ላይ የእግዚአብሄር ልጅ የሚለው ነገር ተጨምሮ እናገኛለን።

ተጨማሪ አንድ ምሳሌ እንመልከት፡- እየሱስ አምስት ሺ ሰዎችን ካበላ ቡሃላ በማቲዎስ ወንጌል 14፡22 ጀምሮ እየሱስ በባህር ላይ ስለ ሰራው ታሪክ ይተርካል። በ ቁጥር 33 ላይ [ በታንኳይቱም የነበሩት በእውነት የእግዚአብሄር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት። ] ይላል።

ማርቆስ 6፡51-52 ላይ ስናይ ግን [ስለ እንጀራው አላስተዋሉምና ነገር ግን ልባቸው ደንዝዞ ነበር ] ይለናል። እንኳን የእግዚአብሄር ልጅ ብለው ሊሰግዱለት ቀርቶ ተአምራቱን እንኳን ከታንኳይቱ ከወረዱ ቡሃላ እንደተገለጠላቸው ነው ሚነግረን? የትኛውን ትክክል ብለን እንቀበል?? ሁሉንም ጠለቅ ብሎ በዚህ ጽሁፍ ማሳየት አስቸጋሪ ቢሆንም ይህንን እንደፍንጭ ይዘን በደንብ መፈተሽ ግን እንችላለን። መጽሃፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በምእራፉ ግርጌ ላይ ስለዚህ ልዩነት ጽፈዋል። ጆን ፎንቴን በፒልካን አዲስ ኪዳን ትርጉም ላይ በማርቆስ ላይ ያለውን ትረካ የተወው የማቲዎስ ጸሃፊ ሃዋርያቱን ጥሩ እይታ የተሰጣቸው ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ስላቀረበ እንደሆነ ይገልጻል። ( ገጽ 35) በ 1988 የሃርፐር እትም ላይ ገጽ 967 ላይም ማቲዎስ እየሱስን የአምላክ ልጅ ለማረግ መጣሩን እና ከማርቆስ መቃረኑን ይነግረናል። በአጭሩ እየሱስም ሆነ ተከታዮቹ አምላክ መሆኑን በእርግጥ ሲመሰክሩ አናይም።

# ❖ ነጥብ ሶስት፡- ቁርዐንስ ምን ይላል?

ከአለም ታላላቅ ሀይማኖቶች ውስጥ አንዱ የሆነው እስልምና ስለ እየሱስ በቁርአን ምን እንደሚል በጥቂቱ እንዳስሳለን።ከሌሎች እምነቶች በተለየ በእስልምና እየሱስ(ዐሰ) ትልቅ ቦታ አለው። እስልምና እየሱስ መሲህ እና ለእስራኤላውያን የተላከ የተከበረ ነብይ እንደሆነ ያስተምራል። ከክርስትና በተቃራኒ እየሱስ ከማርያም የተወለደ የአምላክ አገልጋይ እና ሳይሰቀል ወደ ሰማይ እንዳረገ ያስገነዝባል። ስለ አልመሲህ ኢሳ በቁርአን ውስጥ ምን እንደተባለ ትንሽ እንመልከት፡-

በ ቁርዐን 4፡171 ﴿ እናንተ የመጽሃፍቱ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲህ ኢሳ ፥የአላህ መልእክተኛ፥ ወደመርየም የጣላት (የሁን )ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው። በአላህና በመልእክተኞቹም እመኑ፤ (አማልክት) “ሶስት ናቸው” አትበሉም፤ ተከልከሉ፤ ለናንተ የተሻለ ይሆናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ። 172. አልመሲህ ለአላህ ባርያ ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም፤ ቀራቢዎች የሆኑ መለአክትም፥እርሱን ከመገዛት የሚጠየፍ እና የሚኮራ ሰው፥ሁሉንም በእርግጥ ወደሱ ይሰበስባቸዋል።﴾

# ቁርዐን ምን...

በሱረቱል መርየም በዝርዝር ስለ አወራረዱ ይተርካል።ከ 19፡16-40 ድረስ ስለዚሁ በስፋት ያስሳል። በ ቁጥር 35 ﴿ ለአላህ ልጅ መያዝ አይገባውም፤(ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፤ ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው “ሁን” ነው፥ ወድያውም ይሆናል። ﴾ በሱረቱል ኢምራን 59 የእየሱስ ምሳሌ የአዳም ምሳሌ እንደሆነ ይገልጻል። ሁለቱም አባት የላቸውም። ሁለቱም በሁን ተፈጥረዋል። እንደባይብልም ካየነው ሁለቱም የእግዚአብሄር ልጅ ተብለዋል።

ቁርዐን 9፡30 ﴿ አይሁድ ኡዘይር የአላህ ልጅ ነው፥አለች ፤ ክርስትያኖችም አል-መሲህ የአላህ ልጅ ነው፥ አሉ፤ ይህ በአፎቻቸው ( የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፤ የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፤ አላህ ያጥፋቸው፤ እንዴት ይመለሳሉ! ﴾

ቁርዐን 10፡68 ﴿አላህ ልጅን ያዘ (ወለደ) አሉ፤ ጥራት ተገባው፤ እርሱ ተብቃቂ ነው፤ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው፤ እናንተ በዚህ( በምትሉት) ምንም አስረጅ የላችሁም፤ በአላህ ላይ የማታውቁት ትናገራላችሁን?

በእስልምና አምላክ አምሳያም ልጅም ቢጤም የለውም። ሱረቱል ኢኽላስ ላይ ይንደተጻፈው።

﴿በል፡- “አላህ እርሱ አንድ ነው። 2. አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። 3.“አልወለደም፤ አልተወለደም። 4. “ለእርሱ አንድም ቢጤ የለውም።”﴾

ስለዚህ በእስልምና አምላክ ልጅ አለው፤ ወይም ሰው ሆኖ ተወልዷል የሚለው አስተምህሮ ተቀባይነት የለውም።

# ጌታ የተባለው እየሱስ ብቻ ነውን?

በዩሃንስ ወንጌል ምእራፍ 20፡28 ላይ ተጠራጣሪው ቶማስ እየሱስን ጌታዬ አምላኬ ብሎታል። ይህ እየሱስ ፈጣሪ አምላክ መሆኑን ያሳያልን? ከዚህ ቀደም እንዳየነው እየሱስ አንድም ጊዜ አምላክ ነኝ ብሎ አያውቅም። ነገር ግን መልእክተኛ እና ነብይ መሆኑን በተደጋጋሚ ጊዜ ተናግሯል። እንዲሁም የዘላለም ህይወት አምላክን በብቸኝነት በማመን እና በሱም መልእክተኝነት በማመን መሆኑን ተናግሯል።በዩሃንስ ወንጌል 17፡3 [እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም እየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘልአለም ሕይወት ናት] ይላል።

ብዙ ክርስትያኖች ዩሃንስ ወንጌል 10፡30ን ጠቅሰው አብ እና እየሱስ አንድ አምላክ ናቸው ይሉናል። ነገር ግን ከ 23 ጀምረን ካነበብነው የአላማ እንጂ የመለኮት አንድነትን እንደማያካትት እንረዳለን።በተጨማሪም እዛው ከዩሃንስ 17፡3 ቀጥለን ካነበብን አንድነታቸው አምላክ ለሱ የሰጠው በጎች የአብም ስለሆነ ፤ አብ ስለሰጠውና ከሱ ሚነጥቅ ስለሌለ ከእየሱስም ከአብም ሚነጥቅ ስለማይኖር በዚህ ረገድ ብቻ አንድ እንደሆኑ ግልጽ ይሆንልናል። ቁጥር 11 ላይ (... እንደ እኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ በስምህ ጠብቃቸው።) የሚለውን ክርስትያኖች እንደሚሉት ዩሃንስ 10፡30 ላይ የመለኮትን አንድነት ካሳየና እየሱስ እና አብ አንድ እንደሆኑት ሃዋርያቱም ከነሱጋ አንድ ከሆኑ ከ 14 በላይ አምላክ ሊኖረን ነው ማለት ነው።

ወደ ዩሃንስ ወንጌል ስንመለስ 10፡30-36 እንዲህ ይነበባል፡- [ እኔና አብ አንድ ነን።አይሁድም ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሱ። እየሱስ። ከአባቴ ብዙ መልካም ስራ አሳየኋቹ፤ከእነርሱ ስለማናቸው ስራ ትወግሩኛላችሁ?ብሎ መለሰላቸው።አይሁድም። ስለ መልካም ስራ አንወግርህም፤ስለ ስድብ፤አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት።እየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። እኔ።አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በህጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሃፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሄር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥የእግዚአብሄር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደአለምም የላከውን።ትሳደባለህ ትሉታላችሁን?]

ከነዚህ አንቀጾች ብዙ ነገር ማወቅ እንችላለን። ለምሳሌ ፦

1) የአምላክ ልጅ እንጂ አምላክ ነኝ አለማለቱን። ራሱን የአምላክ ቃል ከሚመጣላቸው ነብያት ጋር ማወዳደሩ እና እነሱ እራሱ እኔ የአምላክ ልጅ ነኝ ከማለቱ በላይ አማልክት መባላቸውን ማንሳቱ እሱም እንደሌሎች ምልእክተኞች መሆኑን ያሳያል።

2) መልእክተኛ መሆኑን፦ በግልጽ ቋንቋ አብ የቀደሰውን ወደአለምም የላከው ፤ በማለት የእግዚአብሄር አብ መልእተኛ መሆኑን መስክሯል።

3) እየሱስ ባቻ ሳይሆን ሁሉም ነብያት አማልክት እንደሚባሉ፦ይህ ግን ከአምላክ ፈጣሪጋ አንድ ናቸው ወይም እኩል ናቸው ማለት አይደለም። 10፡29 አብ ከሁሉም ሰው ይበልጣል።ከእየሱስም አብ ይበልጣል። ዩሀ.14፡28 (መዝ.ዳዊት 82፡6)

አምላክ ሙሴን አምላክ ማለቱንም እንደተጨማሪ ማስረጃ መውሰድ እንችላለን።ዘጸ.7፡1 እግዚአብሄርም ሙሴን አለው። እይ፥ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለው፤ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል።] ታድያ ሙሴን አምላክ አርጎ እየሱስን ጌታና ክርስቶስ ቢያደርገው ምን ይገርማል?(የሀዋ.ሥራ 2፡36)

ባጠቃላይ በመጽሃፍ ቅዱስ ጌታ እና አምላክ የተባሉት ብዙ ከመሆናቸውም በላይ እየሱስን አምላክ ነው የሚያስብል የተለየ ተአምር የለውም። ከሱ በፊት ያሉት ነብያት ያረጉትን ነገር እሱም እንደነብይ አርጓል።አምላክ ተአምራትን ሰቶ የላከው ሰው ነው።(የሀዋርያት ስራ 2፡22)

{ የመርየም ልጅ ዒሳም፦ “የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥ እና ከእኔ ቡሃላ ስሚመጣው መልእክተኛ ስሙ አህመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደ እናንተ(የተላክሁ) የአላህ መልእክተኛ ነኝ”....} ቁርዐን 61፡ 6

# የአምላክ ማንነት በ ትላልቅ ሀይማኖቶች ምን ይመስላል?

{የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደሆነች ቃል ኑ።(እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በእርሱ ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉ ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤በላቸው። እምቢ ቢሉም፡-እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ በሏቸው።}(ቁርአን 3፡64)

የእስልምና እምነት በፈጣሪ አንድነት አጥብቆ ያምናል። ሌሎቹስ?እስኪ እጅግ በጥቂቱ እንመልከት

1)ሂንዱዊዝም፡-በሂንድዎች የእምነት መጽሃፍ ላይ እንዲህ ይላል።

" ኤካም ኢቫዲያታም" "አንድ ነው ሁለተኛ የለውም"(ቻንድዮጋ ኡፓኒሻድ 6፡2 ፡1)

"ና ካስያ ካሱጅ ጃኒታ ና ካዲፓህ" ጌታም ሆነ ወላጆች የለውም።(ስቬታሳቫታራ ኡፓኒሻድ 6፡9 )

"ና ታስያ ፕራቲማ አስቲ" እርሱን የሚመስል ምንም የለም። (ስቬታሳቫታራ ኡፓኒሻድ 4፡19)

2)ጁዲሂዝም፡- አይሁዶች የሚከተሉት እምነት ሲሆን ከክርስትና በፊት የሚታወቅ እምነት ነው።

"ሻማ ኢስራኤሉ አዶናይ ኢላ ሀይኖ  አድና ኢቫድ" ስማ እስራኤል ሆይ ፤ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው።" ዳግ.6፡4

"እኔ፥እኔ እግዚአብሄር ነኝ፥ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም።" ኢሳያስ 43፡11

"...ከእኔ በቀር አምላክ የለም።..." ኢሳ.45፡5

" እኔ አምላክ ነኝና፥እንደኔም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሄር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም።" ኢሳ.46፡9

(ዘጸ.20፡3-5 ፣ዘዳ.5፡7-9...)

3)ክርስትና፡-ክርስትና በአለም ላይ ወደ 2 ቢልየን የሚጠጉ ተከታዮች ያለው እምነት ነው። የብሉይ ኪዳንን እና አዲስ ኪዳንን መጽሃፍት መሰረት ያደርጋል።

“እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም እየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘልአለም ሕይወት ናት” 17፡3

“ሻማ ኢስራኤሉ አዶናይ ኢላ ሀይኖ  አድና ኢኻድ” ስማ እስራኤል ሆይ ፤ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው።” ማርቆስ 12:29

በዩሃንስ ወንጌል 1፡1-14 መሰረት አድርገው ቃልም ስጋ ሆነ፤ ያ ቃል እየሱስ አምላክ ሆኖ በሰው አምሳል መወለዱን ያሳያል ይሉናል። ነገር ግን ቃልም እግዚአብሄር ነበር የሚለውን ቃል በግሪኩ ባይብል ላይ ካየነው Ton Theos ነው የሚለው።  Ton Theos ከ Ho Theos ይለያል። የመጀመርያው ትናንሽ አማልክትን(gods) ወይም መልእክተኞችን( prophets) ወይም በቀላሉ መለኮታዊ(devine) ማለት ሲሆን Ho Theos ግን ፈጣሪ አምላክን (GOD) ይወክላል። በመጽሃፍ ቅዱስ ton Theos ወይም god የሚለውን ለሙሴ(ዘጽ.7፡1) እና ለ ሰይጣንም( 2 ቆሮ 4፡4) ተጠቅሞታል። ቃላት በአግባቡ አለመተርጎማቸው በመልእክቱ ላይ ትልቅ ተጽእኖ አላቸው።

4)እስልምና፡- የእስልምና ትልቁ ጥሪ ተውሂድ ወይም የአላህ አንድነት ነው። የቁርአን ትልቁ መልእክትም ይሄው ነው። በሱረቱል ኢኽላስ አንድና እውነተኛው አምላክ እሱ ብቻ መሆኑን ይነግረናል። እንዲሁም በ 4፡11 ፣ 2፡225 ፣ 23፡91 ... ስለ አንድነቱ ማወቅ እንችላለን።

# እውነቱን እንዴት ማወቅ እችላለሁ??

እንዳጠቃላይ ስናየው ሁሉም ሃይማኖት የአምላክን አንድነት እና ብቸኝነት ይሰብካሉ። ነገር ግን እውነተኛው እምነት ብቻ ነው ከባእድ አምልኮ እና ብክለት የጸዳው። እውነተኛውን እምነት ለማወቅ ገለልተኛ ሆነን የትኛው እምነት ነው በትክክል እውነተኛውን እምነት እንድናመልክ ሚጋብዘው። የትኛውስ ነው በባእድ አምልኮ የተበረዘው ብለን ማየት አለን።

በዚህ ምድር ላይ ከአንድ በላይ አምላክ ቢኖር ኖሮ አንዱ ከሌላው ለመብለጥ በተፎካከሩና እርስ በእርስ በተጣሉ ነበር።(21፡22)

እውነታውን ለማወቅ ከመጣር በጠጨማሪ እውነተኛው አምላክ ወደትክክለኛው እምነት እንዲመራን መጸለይ አለብን። ካልሆነ አምላክ ጭፍኖችን አይመራም።

# ለተጨማሪ ማብራርያ እውነተኛው የፈጣሪ እምነት ሚለውን መጽሃፍ(Booklet) ያንብቡ።

“እነዚያ << አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲህ ነው>> ያሉ በእርግጥ ካዱ።... ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም።ከሚሉት ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እነዝያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል። (ቁርዐን 5፡72-73)”

# ዋቢ መጽሐፍ


1.Did God Become Man, Bilal phlips

2,Is jesus God?, shair Ally

3,Christianity the origional, Dr.Muhammad bin Abdullah As-Saheem

4,ቅዱስ ቁርዐን የአማርኛ ትርጉም- እነ ሸይኽ ሰኢድ ሙሐመድ ሳዲቅ - 1997 ነጃሺ ማተምያ

5,መጽሐፍ ቅዱስ

6, Concept of God in Major  Religions, Dr.Zakir Abdul-Karim Naik

7, www.Answering Christinity.org


አልሃምዱሊላህ በመጀመርያም በመጨረሻም።


...ተፈጸመ...